# የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት

## የተማሪ መጽሐፍ

## አስረኛ ክፍል


አዘጋጆች:-

ማርታ እሸቱ

ነፃነት ጌትነት

አርታኢ:-

የኋላሸት ደሳለኝ

ገምጋሚዎች:-

መኮንን አስማማው

ተስፋዬ ወ/ሚካኤል

ወርቁ አድማስ



AL GHURAIR
PRINTING AND PUBLISHING LLC

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር



© MoE, FDR Ethiopia
Not to be republished

© MoE, FDRE Authorized Not to be reproduced

## ምስጋና

የዚህ መጽሐፍ ዲዛይን ህትመትና ስርጭት ማከናወኛ ገንዘብ የተገኘው በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ኘሮጀክት (GEQIP) አማካኝነት ነው:: የፕሮጀክቱ ዋና ዓላማ በአገሪቱ በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከ1ኛ-12ኛ ክፍሎች የሚሰጠውን የትምህርት ጥራት ማሻሻል ነው::

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ለGEQIP የዋለውን ገንዘብ ያገኘው በብድር/በእርዳታ ሲሆን ብድሩን/ እርዳታውን የሰጡት ዓለምአቀፍ የልማት ማህበራት (IDA)፣ ፋስት ትራክ ኢንሼትብ ካታሊቲክ ፈንድ (FTI CF) እና ሌሎችም የልማት አጋሮች ማለት የፊንላንድ፣ የኢጣሊያ የልማት ማህበር፣ የኔዘርላንድና የታላቋ ብሪታኒያ የእርዳታ ድርጅት አለምአቀፍ የልማት ዋና ክፍል (DFID) ናቸው::

ሁሉንም በዝርዝር መጥቀስ የማይቻል በርካታ ግለሰቦችና ድርጅቶች ይህ የተማሪ መጽሀፍና የመምህር መምሪያ እውን እንዲሆኑ ያልተቆጠበ ድጋፍቸውን ሰጥተዋል:: በዚህም ትምህርት ሚኒስቴር ምስጋናውን ያቀርባል::

© በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
1ኛ እትም፣ 2004 ዓ.ም
ISBN 978-99944-2-255-5

**የአል-ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት**
**የፖ.ሳ.ቁጥር 5613**
**ዱባይ፣**
**የተባበሩት የአረብ ኤሜሬት**

**ከኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር**
**የፖ.ሳ.ቁጥር 100767**
**አዲስ አበባ**
**ኢትዮጵያ**

ጋር በመተባበር ይህን መጽሐፍ ለኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር አዘጋጅተው አትመው፣ አሰራጭተዋል::

ሁሉም የህትመት መብቶች ተከብረዋል::

የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም እንደማይቻል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 410/2004 የኮፒራይትና የተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ 10ኛ አመት ቁጥር 55 አዲስ አበባ ጁላይ 19, 2004 ይከለክላል::

የስዕሎችን የኮፒ ራይት መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል:: ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን::

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**


መግቢያ .................................................... i

ምዕራፍ አንድ:- ቋንቋና ህብረተሰብ ................................፩

ምዕራፍ ሁለት:- ባሕላዊ ጋብቻ.....................................፲፯

ምዕራፍ ሦስት:- ልቦለድ ........................................... ፴፫

ምዕራፍ አራት:- ማሕበረሰብና ጤና ................................፶

ምዕራፍ አምስት:- ቀና አመለካከት ................................ ፷፮

ምዕራፍ ስድስት:- ግጥም.......................................... ፸፯

ምዕራፍ ሰባት:- የአረጋውያን ሚና............................... ፺፩

ምዕራፍ ስምንት:- ሴቶች በባህል ውስጥ ...........................፻፭

ምዕራፍ ዘጠኝ:- ሱስ ............................................ ፻፲፱

ምዕራፍ አስር:- ሥራና ምርት.................................... ፻፴

ሙዳየ ቃላት...................................................፻፵፫

ፈሊጣዊ አነጋገሮች ከነፍታቸው ................................ ፻፵፭

ዋቢ መጻሕፍት ..................................................፻፵፮


© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

# መግቢያ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎች የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ማጐልበትና የሥነጽሑፍና የሥነልሳን እውቀትን ማዳበር ናቸው:: እነዚህ ዓላማዎችም በመርሀ-ትምህርቱ ላይ በግልጽ ሰፍረው ይገኛሉ::

የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ ከሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች መካከል ግንባር ቀደም ተጠቃሽ የመማሪያ መጽሐፍ ነው:: የተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ ደግሞ በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች በየጊዜው ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ ይችላል:: አንደኛው የመርሐ ትምህርቱን አላማዎች በማስፈፀም ረገድ የመፅሐፉን አቅም ለማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ መርሀ ትምህርቱ ላይ ማሻሻያ ወይም ለውጥ ሲደረግ ነው::

ይህ የ፲ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ በአዲስ መልክ እንዲዘጋጅ የሆነበት ምክንያትም በ፳፻፩ ዓ.ም. መርሀ ትምህርቱ እንዲሻሻል በመደረጉ ነው:: መጽሐፉ መርሀ ትምህርቱ ትኩረት የሰጠባቸውን ጉዳዮች ሙሉ በሙሉ እንዲያካትት ጥረት ተደርጓል:: ምንባቦቹ ማብራሪያዎቹና መልመጃዎቹ መርሀ ትምህርቱን መነሻ በማድረግ በክሂልና በእውቀት ዘርፍ ተደራጅተው ቀርበዋል::

ምንባቦቹና ማብራሪያዎቹ፣ ግልፅና ሳቢ፣ መልመጃዎቹ ደግሞ አሳታፊ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል:: በየምእራፉ ማብቂያ ዐበይት ነጥቦች በማጠቃለያ መልክ ከመቅረባቸውም በላይ፣ ተማሪዎች የየምዕራፉን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ የሚያመሳክሩባቸው የግንዛቤ ማመሳከሪያ ነጥቦች ተዘጋጅተዋል:: ተማሪዎች በነዚህ ነጥቦች እየተመሩ የትምህርቱን ዓላማዎች በመፈፀም ረገድ በራሳቸው ያሉበትን ደረጃ መገምገምና ጉድለቶቻቸውን ማስተካከል ይጠበቅባቸዋል:: በመሆኑም መጽሐፉ ትምህርቱን በሚፈለገው መንገድ ለመከታተልና የትምህርቱን ዓላማዎች ለመጨበጥ ያስችላል ተብሎ ይታመናል::

በመጨረሻም ለመጽሐፉ ዝግጅት ጽሑፎቻቸውን ያዋሉንን ሁሉ እያመሰገንን፣ ስለመጽሐፉ ከመምህራን፣ ከተማሪዎችና ከሌሎች የህብረተሰቡ ክፍሎች የሚቀርቡ አስተያየቶችን ለመቀበል ዝግጁ መሆናችንን እንገልፃለን::

© MoE, FDRE Ethiopia
Not to be reproduced